24 ሴፕቴምበር 2018

# የሰሜን ኮሪያ ጥርቅም ኩባንያዎች እና የማዕቀብ ጥሰቶች በአፍሪካ

በካትሪን ክራንዝ /Kathrin Kranz/፤ PhD

## 1. *መግቢያ*

ጥርቅም ኩባንያዎች በተለያዩ በርካታ ፋብሪካዎች ዉሕደት የተመሰረቱ ኩባንያዎች ናቸው።[1] የሰሜን ኮሪያ ጥርቅም ኩባንያዎች በደንብ የተደራጁ እና የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው፤ እንዲሁም የተወሳሰቡ የማዕቀብ ጥሰት ዘዴዎች ያሏቸው ናቸው። በመሆኑም በቅርቡ የወጣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኤክስፐርቶች ቡድን ሪፖርት ሰሜን ኮሪያ (DPRK) "የጦር መሳሪያ ማእቀቡን መጣስ እንደቀጠለች እና ጠንካራ የገንዘብ ማእቀብ ሊጣልባት እንደሚገባ ጥብቅ ድምዳሜ ላይ ደርሷል፤ የማእቀቡ ቀጠና በሰፋ ቁጥር የማጭበርበሩም መጠነ-ርዕይ የዚያኑ ያሕል እንደሚሰፋ" ዘገባው አመልክቷል።[2] እነዚህ የማእቀብ ጥሰት እንቅስቃሴዎች ሊቀጥሉ ይችላሉ። በርግጥ፤ በሰሜን ኮሪያ ላይ አጠቃላይ ማእቀቦችን ማስቀጠል ጭራሽ የጥርቅሞቹን ኩባንያዎች ሐይል እና ተሰሚነት ያብሰው ይሆናል።[3] ስለዚህ፤ የሰሜን ኮሪያ ኩባንያዎች ህብረቶች የሚጣሉባቸዉን ማእቀቦች ለማምለጥ የሚጠቀሙባቸውን ዘዴዎች መረዳት አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። እነዚህ ዘዴዎች የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ግለሰቦች እና ኩባንያዎች የሚጠቀሙባቸውን ተለዋጭ ስሞች፣ የዲፕሎማቶችን፣ የኢምባሲዎችንና የኢምባሲ ሠራተኞችን ጉዞዎች፣ እንዲሁም ሰሜን ኮሪያ (DPRK) በሌሎች አገሮች የገነባቻቸዉን ያልተማከሉ የኩባንያ ሞዴሎችንም ይጨምራሉ። በእነዚህ ዘዴዎች ላይ የተሻለ ግንዛቤ መጨበጥ በማዕቀቦች ጥሰት ላይ የሚደረገዉን መከላከል ቀላል ከማድረጉም በተጨማሪ የማእቀብ ጥሰቱን ለመከላከል መንግስት የሚያወጣዉን ወጪም ይቀንሳል።

## 2. የሰሜን ኮሪያ ጥርቅም ኩባንያዎች

የሰሜን ኮሪያ ጥርቅም ኩባንያዎች 'የግል ሕዝባዊ አጋሮች' እየተባሉ ይሞካሻሉ።[4] በሰሜን ኮሪያ ሕግ መሰረት፤ መንግስት ዋናው የኢኮኖሚው አንቀሳቃሽ እና የሁሉም ኩባንያዎች ባለቤት ነው። ኩባንያዎች ባመዛኙ በግል ሲመሩ እና በከፊል ከሰሜን ኮሪያ ተጽእኖ ነጻ ሆነው በግል ፋይናንስ ሲደጎሙ ከመንግስት ጋር ያለውን ግንኙነት መገንዘብ ይጠቅማል፤[5] ምክንያቱም በዚህ ጽሁፍ በክፍል ሦስት እና አራት እንደተገለጸው ማዕቀቦቹን ለመጣስ በሰሜን ኮሪያ የሚደረገውን አማራጭ መጠን ያሳያልና።

ከ 2014 ዓ.ም ጀምሮ የመንግሥት ፋብሪካዎች ሰሜን ኮሪያውያን ማናጀሮች ከዉጪ ዜጎች ጋር እንዲነግዱ እና የጋራ ይዞታ እንዲመሰርቱ የተፈቀደላቸው መሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ነው።[6] ይህ ጉዳይ የሰሜን ኮሪያ ጥርቅም ኩባንያዎችን በማግኘት እና እንቅስቃሴያቸውን በመፈተሽ ረገድ ያሉት የበለጠ መወሳሰቦች ባለምአቀፍ ደረጃ በሚፈጥሩት የዉጪ ንግድ መረብ እና የጥርቅም ኩባንያዎቹ በውጪ የሚንቀሳቀሱ አጋሮች ላይ የሚንፀባረቅ ነው። የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ኩባንያዎች ማእቀቦችን ለመጣስ በሌሎች አገራት ኩባንያዎች ዉስጥ የሚነድፏቸው ሥልቶች በዚህ መልኩ መጤን አለባቸው።

በተጨማሪም፤ በሰሜን ኮሪያ ኩባንያዎች ላይ ማእቀብ ተጠናክሮ በተጣለ መጠን ማዕቀቡን ለማለፍ የሚደረገው ማታለልም የዚያኑ ያህል ይጨምራል። ባለሙያዎች እንደሚገምቱት፤ ትናንሽ እና መካከለኛ ኩባንያዎች ማእቀቦቹን በማጭበርበር ለማለፍ አቅም የሌላቸው ለዚህ ነው።[7] የአነስተኛ እና የመካከለኛ ኩባንያዎች እንቅስቃሴ በአያሌው ተገድቧል። በምላሹም፣ የሰሜን ኮሪያ የንግድ እንቅስቃሴ ትኩረት ወደ ጥርቅም ኩባንያዎች እና ለኢኮኖሚው የሚሰጡትን ድጋፍ

ወደማሳደግ ሳይዞር አይቀርም። በዉጤቱም ሰሜን ኮሪያ (DPRK) በዉጭ ሃገራት የገንዘብ ክምችቷን ለመጠበቅ ማእቀቦችን ለማምከን የምታደርገውን ጥረት ታጠናክር ይሆናል።

ሰሜን ኮሪያ በአፍሪካ (በሌሎችም) የምታደርገውን እንቅስቃሴ ይበልጥ ለመረዳት የሚያግዙ ወሳኝ የሆኑ ጥርቅም ኩባንያዎች ቀጥሎ ቀርበዋል።

## 2.1 ግሪን ፓይን የተባበሩት ኩባንያ (Green Pine Associated Corporation)/የኮሪያ ማዕድን ልማት ንግድ ኩባንያ (ኮሚድ /KOMID/)

ግሪን ፓይን /Green Pine/ የተባበሩት ኩባንያ (Green Pine) ኮሪያ ማዕድን ልማት ንግድ ኩባንያ (KOMID)፤ ኮሚድ ኤፕሪል 24፣ 2009 ዓ.ም ከተቋቋመ በኋላ፤ ተክቶታል። ግሪን ፓይን ሜይ 2፣ 2012 ዓ.ም ነበር በማዕቀብ ዝርዝር ውስጥ የገባው።[8] ግሪን ፓይን /Green Pine/ ኮሚድ /KOMID/ ከተምዘግዛጊ ሚሳይሎች እና የጦር መሳሪያዎች ጋር የተያያዙ እቃዎችን ላኪ የሆነ ዋና የጦር መሳሪያ ደላላ ነው።[9] የሰሜን ኮሪያ ዋና የዉጪ ስለላ ድርጅት በሆነው በሪኮናይዛነስ ጠቅላይ ቢሮ /Reconnaissance General Bureau/ አመራር ስር ይንቀሳቀሳል።[10]

ግሪን ፓይን /Green Pine/ እና ኮሚድ /KOMID/ በፊት በዉጩ አገር የሚሰሩ በርካታ ተባባሪ አካላት ያሉት እና በቀጥታ የጥርቅሙ አካል ከሆኑ እና ካልሆኑ ከሌሎች ኩባንያዎች ጋር ተባብሮ የሚሰራ ነው። በግሪን ፓይን /Green Pine/ ኮሚድ /KOMID/ ጥርቅሞች እና ከእንቅስቃሴያቸው ዉስብስብነት አንጻር ግሪን ፓይን/ኮሚድ የዘረጋቸውን ሌሎች መረቦችንም መገንዘብ ይጠቅማል።

ለምሳሌ፤ ኮሚድ /KOMID/ ከማኑሱዴ የባህር ማዶ ፕሮጀክት የኩባንያዎች ግሩፕ /Mansudae Overseas Project Group of Companies (Mansudae)/ ከሚባለው የሰሜን ኮሪያ (DPRK) የግንባታ ኩባንያ ጋር ይተባበራል። ማንሱዴ /Mansudae/ ቢያንስ ከ 14 የአፍሪካ አገሮች ጋር “ከፋብሪካ እስከ ቤተመንግስት ግንባታ በሁሉም የግንባታ ሥራዎች ላይ ይሳተፋል።”[11] ማንሱዴ /Mansudae/ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በናሚቢያ ዋና መስሪያ ቤት ነበረው። ዋና ሥራ አስኪያጁ ኪም ቶንግ ቾል ነበር (ኪም ቶንግ ቾል የባህር ማዶ የዉጪ ንግድ ባንክ ተወካይም ነበር)።[12] ሠራተኞችን ከሰሜን ኮሪያ (DPRK) አልጄሪያን፣ አንጎላን፣ ቦተስዋናን፣ ቤኒኒን፣ ቻድን፣ ኮንጎ ድሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን፣ ኢኳቶሪያል ጊኒን፣ ሞዛምቢክን፣ ናሚቢያን፣ ቶጎን፣ እና ዚምቧቤን ጨምሮ ወደ ሌሎች አገራት በማጓጓዝ እና ጉዞዎችን በማቀለጣጠፍ በጸጥታው ምክር ቤት ኦገስት 5፣ 2017 ዓ.ም ተመዝግቧል።[13] ኮሚድ /KOMID/ እና ማንሱዴ /Mansudae/ በጋራ፤ ናሚቢያ ውስጥ ፋብሪካ በመገንባት ተሳትፈዋል።

የኮሚድ የገንዘብ ተቋምም እንዲሁ ከማእቀብ ጥሰት ጋር ንክኪ ባላቸው ተቋማት ይታገዛል። Tanchon ንግድ ባንክ (በፊት Changwang የብድር ተቋም ይባል የነበረው፤ FKA: ኮሪያ ቻንግዋንግ የብድር ባንክ) የካሚድ ዋናው የገንዘብ ክንድ ነበር።[14] አምሮጋንግ ልማት ባንክን /Amroggang Development Bank/ እና በኮሚድ /KOMID/ ስም የገንዘብ ዝውውር የሚያካሂደውን ኮሪያ ክዋንግሶን የባንክ ኩባንያን /Korea Kwangson Banking Corporation/ ጨምሮ ከሌሎች በማዕቀብ ዝርዝር ውስጥ ካሉ በርካታ አካላት ጋር ይያያዛል።[15]

ግሪን ፓይን እንደ የተፈጥሮ ሐብት ልማት /Natural Resources Development/ እና የከበሩ ማእድናት ጠቅላላ ኩባንያ /Investment Corporation of General Precious Metal/ ያሉ ተለዋጭ ስሞችን በመጠቀም ይሰራል።[16] ግሪን ፓይንን በማገዝ የምስራቅ አገር ባንክ /Bank of East Land/ የጦር መሳሪያ ነክ ግብይቶችን ያቀለጣጥፋል። “ማእቀቡን በዘዴ እያመለጠ ገንዘብ በማዘዋወር ከግሪን ፓይን ጋር አብሮ እንደሚሰራ”[17] ኦክቶበር 29፣ 2014 ዓ.ም ተመዝግቧል። የግሪን ፓይን ፕሬዝዳንት ወደ አንጎላ፣ ግብጽ እና ኢራን እስላማዊ ሪፐብሊክ የተጓዘው ሪ ሃክ ቾል ነው። ማእቀቡ እንዲህ ኣይነት እንቅስቃሴዎችን የሚከለክል ቢሆንም ተግባሩ አልተገታም።[18]

Enrico Carisch
ስልክ ቁጥር: (610) 390 9541
2142
Rico.carisch@comcapint.com

www.comcapint.com
110 West 94 Street 2-D
New York፣ NY 10025

Loraine Rickard-Martin
ስልክ ቁጥር፡ (917) 715
loraine።rickard-martin@comcapint.com

## 2.2 የውጪ ንግድ ባንክ

የውጪ ንግድ ባንክ እንደ የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ዋና የውጪ ምንዛሪ ባንክ የሚሰራ መንግስታዊ ባንክ ነው። ለኮሪያ ክዋንግሶን የባንክ ኩባንያ (KKBC) በሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ ኦገስት 5፣ 2017 ዓ.ም ተፈርጇል። KKBC በተፈረጁት ግለሰቦች እና አካላት ዝርዝር ውስጥ ማርች 2 2016 ዓ.ም ተካተተ፤ ይህ የሆነው የኮሚድ ቀኝ እጅ የሆነውን ታንቾን ንግድ ባንክን እና ኮሪያ ሂዮክሲን የንግድ ኩባንያን በገንዘብ በመደገፉ ነበር፤ ይህም የሰሜን ኮሪያን የኒውክሊየር ጦር መሳሪያ ፕሮግራምን እንደ መርዳት ተቆጥሯል።[19]

## 2.3 ኦሽን የባህር ትራንስፖርት አስተዳደር ኩባንያ /Ocean Maritime Management Company/

ኦሽን የባህር ትራንስፖርት አስተዳደር ኩባንያ (OMM) በባህር ላይ ሕገወጥ ሥራ ውስጥ በተፈረጁ ግለሰቦች፣ አካላት እና ሌሎች ድርጅቶች ዝርዝር ውስጥ ጁላይ 28፣ 2014 ተካተተ፣ ይህም የተደበቀ የጦር መሳሪያ እና ተዛማጅ ቁሳቁሶችን ጭነት በማመቻቸት ላይ በነበረው ሚና ምክንያት ነው።[20] OMM ከመፈረጁ በፊት የመሬት እና የባሕር ትራንስፖርት ሚኒስቴር እጅግ ታላቁ አስጫኝ ኢንተርፕራይዝ ነበር። OMM በኤሽያ፣ በአዉሮፓ፣ በደቡብ አሜሪካ እና በመካከለኛው ምሥራቅ በሚገኙ ቢሮዎቹ ሰፊ መረብን ዘርግቷል። ማዕቀብን በመፍራት ምዝገባቸው በየጊዜው ከሚለዋወጥ 35 መርከቦች ጋር ይሰራል።[21]

## 3. ቁልፍ የማዕቀብ ጥሰቶች በአፍሪካ

የተለያዩ የማዕቀብ ጥሰቶች በተባበሩት መንግሥታት እና በሚዲያ አዘጋገብ መሰረት መሰነድ/ፋይል ሊደረጉ ይችላሉ። ይህ ክፍል በሦስት አበይት ጥርቅም ኩባንያዎች (የጉዳዮቹን ውስብስብነት ከግምት በማስገባት፤ በ ኮሚድ /KOMID/ እና በግሪን ፓይን /Green Pine/ የተደረጉ ክንዋኔዎች ለየብቻ ለውይይት ቀርበዋል) የተፈጸሙ ዋና ዋና ጥሰቶችን ይዘረዝራል። የተለያዩ ጥርቅሞች ተግባራት እና ተወካዮች እንደሚወራረሱ መገንዘብ ያስፈልጋል። የጉዞ እገዳዎችን፣ የመሳሪያ ክልከላዎችን፣ የወታደራዊ ትብብሮችን፣ የንግድ እና የገንዘብ ማዕቀቦችን ጨምሮ የተለያዩ ማዕቀቦች ተጥሰዋል።

## 3.1 ኮሚድ /KOMID/ \ ግሪን ፓይን /Green Pine/

### 3.1.1 ኮሚድ /KOMID/

#### 3.1.1.1 ናሚቢያ

ኮሚድ /KOMID/ የማንሱዴ የባህር ማዶ ፕሮጀክት ግሩፕ ሀሰተኛ ስሞችን በመጠቀም ቁልፍ አካላትን ለናሚቢያው ኦማይትስ የጥይት ፋብሪካ ግንባታ ሰጥቷል።[22] ማንሱዴ /Mansudae/ ከሰሜን ኮሪያ (DPRK) የቀን ሰራተኞችን ተጠቅሟል። የወታደራዊ አካዳሚዉንና የመከላከያ ሚኒስቴር ዋናዉን መስሪያ ቤት ጨምሮ ማንሱዴ /Mansudae/ በበርካታ የወታደራዊ ግንባታዎች ላይ መሳተፉን ናሚቢያ አረጋግጣለች፤ ሆኖም በማንሱዴ /Mansudae/ እና በኮሚድ /KOMID/ መካከል ግንኙነት መኖሩን እንደማታውቅ አስታውቃለች።[23]

በተጨማሪ፤ ኮሚድ /KOMID/ ለናሚቢያ ለወታደራዊ ፈነጂዎችና ፕሮፔላንት ማምረቻ የሚያገለግሉ የተለያዩ እምቅ ታንኮችንና ማሽነሪዎችን ሰጥቷል።[24]

Enrico Carisch
ስልክ ቁጥር: (610) 390 9541 2142
Rico.carisch@comcapint.com

www.comcapint.com
110 West 94 Street 2-D
New York፣ NY 10025

Loraine Rickard-Martin
ስልክ ቁጥር፡ (917) 715
loraine።rickard-martin@comcapint.com

በደቡብ አፍሪካ የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ኢምባሲ በናሚቢያ የባንክ አካዉንት የከፈቱ የኮሚድ /KOMID/ ባለሥላጣናትን ረድቷል።[25]

### 3.1.1.2 ኡጋንዳ

ኮሚድ /KOMID/ ለኡጋንዳ ወታደራዊ እና ፖሊስ ሃይል በተለይም ለኡጋንዳ አየር ሃይል ሥልጠና ሰጥቷል።[26] እነዚህ ድርጊቶች በሰሜን ኮሪያው (DPRK) ዜጋ በሆነው እና በተፈረጀው ግለሰብ በ Ryu Jin ይደገፉ ነበር። የተጣሉበትን ማዕቀቦች አጭበርብሮ ለማለፍ የቶሶንግ ቴክኖሎጂ የንግድ ኮረፖሬሽንን እና ታንቾን ንግድ ባንክን በደጋፊነት ይጠቀምባቸው ነበር። በሐሰት ስም ይዘዋወር እንደነበር ይታመናል።

በካምፓላ ኡጋንዳ የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ኢምባሲ የሚሊታሪ አታሼ ቢሮ የተከለከሉ የወታደራዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት ሞክሮአል።[27]

### 3.1.1.3 ሱዳን

በሱዳን ሁለቱ የኮሚድ /KOMID/ ባለሥልጣኖችን ብናይ፣ ኪም ሶንግ ቾል፤ ኪም ሃክ ሶንግ፤ በሚል ሐሰተኛ ስም የሚጠራ ሲሆን ሶንግ ጆንግ ሕዮክ፤ ደግሞ ሶን ሚን፤ በሚል ሐሰተኛ ስምም ይጠቀማል።[28] ሁለቱም ከዋኞች ከዚህ በፊት ከግብጽ ተባረዋል፤ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባለሙያዎች ምርመራ ዘገባ መሰረት በሱዳን እና በሰሜን ኮሪያ (DPRK) መካከል አገናኝ ማእከላት ሆነው ይሰሩ ነበር። ኮሚድ /KOMID/ የሱዳን መንግስት ከሚቆጣጠረው የወታደራዊ ኢነዱስትሪ ጋር ግንኙነት እንደነበረው የክሱ ሰነድ ያመለክታል። በተጨማሪ፤ ከኮሚድ /KOMID/ ጋር የሚገናኙ ከሰሜን ኮሪያ (DPRK) ወደ ሱዳን የሚሄዱ በርካታ የአየር እና የባህር ጭነቶች እየተመረመሩ ናቸው።[29]

ሰሜን ኮሪያ (DPRK)ም እንዲሁ 122 ሚ.ሜ ፕሪሲዥን ጋይድ የሮኬት መቆጣጠሪያ ክፍሎች እና 80 የአየር ጥቃት ሳተላይት ሚሳይሎች ለሱዳን ማስተር ቴክኖሎጂ ኢንጂነሪንግ ኩባንያ ሰጥቷል። የሽያጩ ኮንትራቶች በኮሚድ /KOMID/ ፕሬዝዳንት Kang Myong Chol (ሐሰተኛ ስሙ Pak Han Se) ተፈርመዋል። Chosun Keunchon Technology Trade Company የተባለውን በመጠቀም ነበር ፊርማዎቹ የተፈጸሙት።[30] በመሆኑም Kim Song Chol፤ ከግብጽ በ13 የ KOMI ሰራተኛ አባላት ታጅቦ ወደ ሱዳን ተጉዟል።[31]
የዩኤስ ዲፓርትመንት ግምጃ ቤት ሚዲያ እንደዘገበው የኮሚድ /KOMID/ ተወካይ Jang Song Chol ሱዳን ውስጥ ቁሳቁሶች ከሚገዙት ግለሰቦች ጋር ይሰራል።" በተጨማሪም በሱዳን እና በሰሜን ኮሪያ መካከል የውትድርና ግንኙነቶችን መኖራቸውን የሚጠቁም ነው።[32]

## 3.1.2 ግሪን ፓይን /Green Pine/

### 3.1.2.1 አንጎላ

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤክስፐርቶች ቡድን በአንጎላ ዉስጥ በግሪን ፓይን ስም የተንቀሳቀሱትን እና ቀደም ሲል በተከለከሉ የጦር መሳሪያ ነክ ጉዳዮች ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸዉን የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ዲፕሎማቶችን መርምረዋል።[33]

የኤክስፐርቶቹ ቡድን ምርመራዉን ቀጥሎ የአንጎላ ፕሬዝዳንት ጠባቂዎች በግሪን ፓይን ስም በሚሰሩ የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ባለሙያዎች እና ዲፕሎማቶች ስልጠና እንደተሰጣቸው አይቷል። ኪም ሕዮክ ቻን የተባለ አንድ ዲፕሎማት ማዕቀቡን በመጣስ ለአንጎላውያን የባህር መርከቦች ጠጋኝ ሆኖ ተሹሞ ነበር።[34] የግሪን ፓይን ተወካይ ከሆነው ከጆን ቾል ያንግ ጋር በመሆን ወደ ሲሪላንካ ለውይይት ሦስት ጊዜ ተጉዟል።

Enrico Carisch
ስልክ ቁጥር: (610) 390 9541
2142
Rico.carisch@comcapint.com

www.comcapint.com
110 West 94 Street 2-D
New York፣ NY 10025

Loraine Rickard-Martin
ስልክ ቁጥር፡ (917) 715
loraine።rickard-martin@comcapint.com

ግሪን ፓይን የወታደራዊ ቅኝት ጀልባዎችን እስከ 2012 ዓ.ም ድረስ ለሀገሪቱ መስጠቱን አንጎላ ዘግባለች። የቻይና ጉምሩክ መዛግብትም እንዲሁ ከግሪን ፓይን ጋር ግንኙነት የነበራቸው ቤጂንግ ሰራሽ ኩባንያዎች የጀልባ ኢንጂኖችን፣ ሞተሮችን እና የራዳር ሲስተሞችን ጨምሮ የባህር መገልገያ ምርቶችን ለአንጎላ መሸጣቸውን ያሳያሉ። በፌብሩዋሪ እና በጁላይ 2011ዓ.ም፤ አውስትራሊያዊው Josef Schwartz ግሪን ፓይንን የወታደራዊ ቅኝት ጀልባዎች እና የመርከብ ቁሳቁሶችን ለአንጎላ እንዲያቀርብ ረድቶታል።[35][36]

### 3.1.2.2 ግብጽ

የግሪን ፓይን የውሸት ስም የሆነው Saeng Pil Trading ኩባንያ ካይሮ ውስጥ እየሰራ ነበር። አንድ An Jong Hyuk የተባለ የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ዲፕሎማት፣ የኩባንያው ተወካይ ሆኖ ከተሾመ በኋላ፣ በዲሴምበር 18፣ 2013 ዓ.ም የኮንትራት ዉሎችን መስጠትንና የባንክ ንግድ ማካሄድን ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት የንግድ ሥራዎችን እንዲሰራ ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር።[37]

### 3.1.2.3 ኤርትራ

የኤክሰፐርቶቹ ቡድን በግሪን ፓይን እና በመንግሥታዊ ጋራዦች (መሳሪያዎችን በሚጠግኑ እና በሚያድሱ) መካከል ግንኙነት መኖሩን አረጋግጧል።[38]

### 3.1.2.4 ሞዛምቢክ

የኤክስፐርቶቹ ቡድን በ 2012 ና በ2017 መካከል ስለተደረጉ ጉዞዎች መረጃ አግኝቷል። ጉዞዎቹ በሞዛምቢክ እና በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ዉስጥ በኮሚድ /KOMID/ እና በግሪን ፓይን /Green Pine/ ስም በሚሰሩ ከጦር መሳሪያ ንግድ እና ዝውውር ጋር ግንኙነት ባላቸው አምስት የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ዜጎች እንደተደረጉ መረጃ ነበረው።[39]

### 3.1.2.5 ዚምባብዌ

የኤክስፐርቶቹ ቡድን በዚምባብዌ ውስጥ ከግሪን ፓይን ጋር የተያያዙ እና ከጦር መሳሪያ ንግድ ጋር ንክኪ ያላቸውን የሰሜን ኮሪያ (DPRK)ን ድርጊቶች እየመረመረ ነው።[40]

## 3.2 የዉጪ ንግድ ባንክ

### 3.2.1 ቱኒዚያ

የውጪ ንግድ ባንክ ወኪሎች 'ካርቶስ /Kartos/' የተባለ የፊት ለፊት ስም ለኩባንያው በመስጠት በቱኒዚያ አረብ ባንክ የአካዉንት ተጠቃሚዎች ሆኑ።[41] Ri Chun Song፤ የተባለ አንድ የባህር ማዶ ንግድ ወኪል ለአሜሪካ ዶላር እና ለዩሮ አካዉንቶች በተመሳሳይ ባንክ ፎርማዉን አኑሯል። የዩሮው አካዉንት የተከፈተው "የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ሚሽን በትሪፖሊ የዋና ጸሐፊው ወኪል" በመሆን በቹን ሶንግ ስም ነው። አሁን ሁለቱም አካውንቶች ተዘግተዋል።

Enrico Carisch
ስልክ ቁጥር: (610) 390 9541
2142
Rico.carisch@comcapint.com

www.comcapint.com
110 West 94 Street 2-D
New York፣ NY 10025

Loraine Rickard-Martin
ስልክ ቁጥር: (917) 715
loraine።rickard-martin@comcapint.com

### 3.2.2 ሊቢያ

በሊቢያ የውጪ ንግድ ባንክ /Foreign Trade Bank/ ዋና ተወካይ፣ ኩ ጃ ሂዮንግ፣ ወደ ቱኒዚያ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ እና ሳውዲ አረብያ ከ 2015 እስከ 2017፤ ጉዞ በማድረግ ተሳትፈዋል፣ እንዲሁም ጉዞዎችን ሲያደርጉ የነበሩት በሁለት ፓስፖርቶች ነው።[42] የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ውሳኔዎች 2321 (2016) እና 2270 (2016) አባል ሀገራት በሰሜን ኮሪያ (DPRK) ምትክ ወይም ትዕዛዝ ስር ሆኖ የሚሰራን ግለሰብ እንዲያባርሩ ያስገድዳል።

## 3.3 ኦሸን የባህር ትራንስፖርት አስተዳደር ኩባንያ /Ocean Maritime Management Company/

### 3.3.1 ግብጽ

የ OMM ተወካዮች በሰንላይት ኤጀንሲ ውስጥ ተደብቀው ነበር፣ ይህም እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ በሳይድ ወደብ ነበር። “ኦሺን ኢጂፕት” እና “ኦሺን ማሪታይም ማኔጅመንት ኢጂፕት” የሚሉ ስያሜዎችን ይጠቀሙ የነበረ ሲሆን፣ OMM የሚለው ስም ግን በግብጽ ውስጥ በትክክለኛው መንገድ የተመዘገበ አልነበረም። የ OMM ተወካዮች፣ የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ዜግነት ያላቸውን ጨምሮ ለ OMM መርከቦች የሎጂስቲክስ እና ኦፕሬሽን ድጋፍ አድርገዋል፣ ይህም በስዊዝ ካናል ውስጥ ማለፍን ጨምሮ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ሰንላይት ኤጀንሲ ለ“ቶንጋዬ ሰኢድ ወደብ” እንደተቀባይ አድራሻ ሆኖም ያገለግል ነበር፣ ይህም ከ OMM ጋር ግንኙነት ላላቸው ተቋማት ማለትም ኮሪያ ቶንጊ ወይም ቶንጊ ሶንባንክ እንደ ቅርንጫፍ ቢሮ ሆኖ እንደሚያገለግል ይታያል። ኮሪያ ቶንግሄ ካይሮ ውስጥ ባለው የኮሪያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢምባሲ ውስጥም ቢሮ ነበረው።[43]

## 4. የሰሜን ኮሪያን የማእቀብ ጥሰቶች በማወቅ እና በመከላከል ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

በክፍል ሶስት ላይ የተጠቀሱት የማእቀብ ጥሰቶች ምሳሌዎች ሰሜን ኮሪያ (DPRK) ማእቀቦችን ለማምለጥ ስትጠቀምባቸው የቆዩ የተለያዩ ስልቶችን ለማወቅ ያስችላል — በተጨማሪም እነዚህን ስልቶች መጠቀም የመቀጠሏ እድል ሰፊ ነው።

### 4.1 ተለዋጭ ስሞች

የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ተወካዮች በተደጋጋሚ ማንነታቸውን ለመደበቅ ይችሉ ዘንድ ተለዋጭ ስሞችን ሲጠቀሙ ቆይተዋል፣ ይህም በአለም አቀፍ ጉዞዎች ላይ እንዳይሳተፉ የሚያደርጋቸውን ማእቀብም ለማምለጥ ነው። ለምሳሌ፣ ኮ ቴ ሁን፣ ሱዳን ውስጥ ያለው የታንኮን ንግድ ባንክ ባህር ዘለል ተወካይ፣ ከማርች 2 2016 ጀምሮ ለማዕቀብ በተፈረጁ ግለሰቦች፣ ተቋማት እና ሌሎች ድርጅቶች ዝርዝር ውስጥ ነበር።[44] “ኪም ሚዮንግ ጂ” በሚል ተለዋጭ ስም ወደ ቻይና፣ ኢትዮጲያ እና የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ ተጉዟል።[45]

ልክ እንዲሁ፣ የኩባንያዎች ጥርቅሞችም ሳይታወቅባቸው ከሀገር ውጭ ለመስራት ተለዋጭ ስሞችን ይጠቀማሉ። በዚህ ረገድ ግሪን ፓይን ሊጠቀስ የሚገባው ነው፣ ተለዋጭ ስሞችን ጥቅም ላይ በማዋል የተለያዩ ቢሮዎችን ቻይና ውስጥ ጨምሮ ከፍቷል።[46]

### 4.2 ዲፕሎማቶች፣ ተወካዮች እና ኢምባሲዎች

የጥርቅም ኩባንያዎች ወኪሎች በኢምባሲዎች ውስጥ የሚሰሩ ሲሆን፣ ከዲፕሎማቶች እና የኤምባሲ ሰራተኞች ጋር በቀጥታ ይተባበራሉ፣ እንዲሁም ከሀገር ውጪ ያለን እንቅስቃሴ ለማቀላጠፍ እንደ ዲፕሎማቶች ስም ይሰጣቸዋል።

ለምሳሌ፣ ሚዲያው ሽያጮችን ለማቀላጠፍ ሲባል የኮሚድ /KOMID/ ባለስልጣናት በሰሜን ኮሪያ (DPRK) ኤምባሲዎች ውስጥ እንደሚሰሩ ሪፖርት አድርጓል። እንደ ኒውዮርክ ታይምስ ከሆነ፣ የኮሚድ /KOMID/ ተወካዮች ሶን ጆንግ ሕዮክ ካይሮ ውስጥ ካለው የሰሜን ኮሪያ ኤምባሲ አምባሳደር ፓክ ቾል ኢል ጋር በመተባበር ለአፍሪካ ሀገራት የሰሜን ኮሪያን መሳሪያዎች ለመሸጥ ይሰራሉ።[47] ኤምባሲው ራሱ በሰሜን አፍሪካ ውስን ክፍሎች እና መካከለኛው ምስራቅ ላይ “የቀጠናው የጦር መሳሪያ አከፋፋይ ተደራቢ እና “ድብቅ የሆነ የሰሜን ኮርያ መሳሪያዎች ማሳያ ባዛር እንዲሁም ርካሽ የሶቭየት ወቅት የውትድርና መሳሪያዎች ማሳያ” እንደሆነ ተገልጦ ነበር።[48]

በተጨማሪም ፓናሉ ሰሜን ኮሪያ (DPRK) የግሪን ፓይንን ከሀገር ውጪ ያሉ ተወካዮች እንደ ዲፕሎማቶች ስልጣን እንደሚሰጣቸውም አሳይቷል።[49] አንጎላ ውስጥ ለምሳሌ፣ ኪም ሂዮች ቻን፣ የግሪን ፓይን ተወካይ እና ዲፕሎማት፣ ኮንትራቶችን ሲዋዋል፣ የመለዋወጫዎች ምንጭ በመሆን ሲሰራ እና የአንጎላ ባህር ሀይል የቅኝት ጀልባዎችን አቅርቦት መሟላት ሲከታተል ነበር።[50] የኪም ሆይክ ቻን ጉዳይ ብቸኛ አይደለም። ሁለተኛ ዲፕሎማት የሆነው፣ ጆል ኮል ያንግ፣ በግሪን ፓይን ፋንታ በመሆን የንግድ ስራዎችን ሲያካሂድ እንደነበር መረጃዎች አሉ።[51]

### 4.3 የጉዞ ዝግጅቶች

ጉዞዋቻቸውን እና መዳረሻቸውን ለመደበቅ የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ተወካዮች በብዙ ሀገራት ማለትም እንደ፣ ለምሳሌ፣ ቻይና፣ ኢትዮጲያ፣ የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ፣ ሩስያ፣[52] ውስጥ ትራንዚት ያደርጋሉ እንዲሁም ሶሪያ አረብ ሪፐብሊክ እና ግብጽንም ጨምሮ ከሌሎች ሀገራትም የአየር ቲኬቶችን ገዝተዋል።[53] ባለስልጣናት እና የጥርቅም ኩባንያዎቹ ተወካዮችም ብዙ ፓስፓርቶችን ይዘው የሚንቀሳቀሱ ሲሆን ይህም የማእቀብ ማስከበርን—ማለትም በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ውስጥ ያሉ የፓስፖርት ቁጥሮችን በመጠቀም ለማስፈጸም የሚደረገውን ጥረት—ከባድ ያደርገዋል።[54]

### 4.4 ያልተማከሉ ኮርፖሬት ሞዴሎች

ያልተማከሉ ኮርፖሬት ሞዴሎች የሰሜን ኮሪያ (DPRK) መገለጫዎች ናቸው እናም በሌሎች ሀገሮች ውስጥ ሆነው ከሰሜን ኮሪያ (DPRK) ድርጅቶች ጋር ትብብር ያላቸው ነጠላ ድርጅቶች ከሰሜን ኮሪያ (DPRK) ገንዘብ ላኪዎቻቸው እና የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ዜግነት ሳይኖራቸው ገንዘብ ከሚልኩላቸው ግለሰቦች ራሳቸውን አርቀው ያሳዩ ዘንድ የሚያደርጋቸውን ኔትወርክ ለመፍጠር እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።[55] ለምሳሌ፣ ከላይ ከኮሚድ /KOMID/ ጋር በተያያዘ ውይይት የተደረገበት ማንሱዴ፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የባለሞያዎች ቡድን ከማሌዢያ-ኮሪያ ግሩፕ (MKP) አስር በላይ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው ድርጅቶች ዝርዝር ውስጥ ነበር።[56] ፓናሉ ዝርዝሩ ውስጥ ያሉ እንደ ማንሱዴ፣ MKP የምርመራ ጠቅላላ ቢሮ፣ OMM እና ኮሪያ ክዋንግሶን ባንኪንግ ድርጅት አይነት የጥርቅም ኩባያዎችን ለመለየት ችሏል።

### 4.5 ከፊት ያሉ ድርጀቶች እና ቅርንጫፎች

ካልተማከለ የኮርፖሬት ሞዴል ጋር በተያያዘ፣ ከፊት ያሉ ድርጅቶች የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ድርጀቶችን ማንነት ለመደበቅ ጥቅም ላይ ይውላሉ። ለምሳሌ ግብጽ ውስጥ ያለ የኮሚድ /KOMID/ ቅርንጫፍ በፓክ ቹን II፣ ቀጥተኛ ተሳትፎ ነበር የተመሰረተው፣ ከዚያም በሰሜን ኮሪያ (DPRK) የግብጽ አምባሳደርም ጭምር ነው።[57] ልክ እንደዚሁ፣ ኮሚድ /KOMID/ ቻይና ውስጥ እንደ ቤጂንግ ኒው ቴክኖሎጂ የንግድ ድርጅት አይነት ከፊት ያሉ ድርጀቶችን ከፍቶ ነበር።[58]

### 4.6 የአንድን ድርጅት ማንነት ለመደበቅ ድርጅቶችን በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ መደበቅ

OMM በተለያዩ ሀገራት ውስጥ የሚሰሩ ተቋማት አሉት። እነዚህ ድርጅቶች ህጋዊ በሆነ መንገድ የሚሰሩ ድርጅቶች አይደሉም። ነገር ግን፣ ከ OMM ጋር ያላቸው ግንኙነት ለመደበቅ በሌሎች ሀገር በቀል ድርጅቶች ውስጥ የተደበቁ ናቸው።[59] ይህ ስልት፣ የድርጅት ተወካዮችን ከአንድ ድርጅት እና ሀገር ወደ ሌላው በማዘወር እንዲሁም ለተወካዮች የዲፕሎማቲክ ማንነትን በመስጠት የሚታገዝ ነው።

### 4.7 ሰላማዊ ሀገራት

የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ማእቀብ ጥሰት ወዳጅ በሆኑ ነገር ግን ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነን ድጋፍ ለሚሰጡ ወይም ለሰሜን ኮሪያ አንቅስቃሴዎች ጆሮ ዳባ ልበስ በሚሉ ሀገራትም እገዛ ያገኛሉ።

ግብጽ በተለይ የሰሜን ኮሪያ (DPRK) የቅርብ አጋር እንደሆነች እንዲሁም የሰሜን ኮርያ ግልጽ ደጋፊ እንደሆነች ታይታለች።[60] የኮሚድ /KOMID/ ባለስልጣናት በራሺያ ውስጥም እንቅስቃሴ እንዳላቸው ታይቷል፤[61] በተጨማሪም ከባህር ዳርቻ ባሉ የውጪ ንግድ ባንክ ተወካዮች ውስጥም እንቅስቃሴ አላቸው፣ ኪም ቶንግ ቾል ቻይና ውስጥ ይገኝ ነበር (ይህም ከፍረጃው በኋላ ነው)።[62]

### 4.7 የውጪ ሀገር ሰዎችን መጠቀም

ለሰሜን ኮሪያ (DPRK) ድጋፍ ሲያደርጉ የታዩ ግለሰቦች አሉ ይህም ያለ ሀገሮቻቸው ድጋፍ ማእቀቦችን ለማምለጥ የሚደረጉ ስራዎች ናቸው። አንድ ሊጠቀስ የሚገባው ምሳሌ፣ የኦስትሪያ ዜግነት ያለው ጆሴፍ ሽዋርትዝ /Josef Schwartz/ ነው፣ ይህም በድርጅቱ በ Schwartz Motorbootservice & Handel GmbH በኩል አንጎላ ውስጥ ላሉ የጥበቃ ማድረጊያ ጀልባዎች እቃዎች መላኩ ነው።[63] ሽዋርትዝ ከሰሜን ኮሪያ (DPRK) ጋር በተለያዩ ወቅቶች ላይ ንግድ ውስጥ ነበር፣ ይህም የቅንጦት እቃዎችን እግድን መጣስንም ጨምሮ ነው።

## 5. ምክረ ሃሳቦች

### 5.1 በጉዞ ዶክመንቶች እና ዝግጅቶች ላይ ጥብቅ ክትትል ማድረግ

በክፍል 4.3 ላይ እንደተጠቀሰው በተቋማት ምትክ የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ባለስልጣናት ከአንድ በላይ ፓስፖርት ይዘው ሲጓዙ የነበረበት ጊዜ ይጠቀሳል። እናም አንድ ባስልጣን የሚጓዝበት ፓስፖርት በተባበሩት መንግስታት ጸጥታ ቢሮ ማእቀብ ዝርዝር ውስጥ ባለው የፓስፖርት ቁጥር ላይሆን ይችላል። እናም ከአለም አቀፍ ጉዞ የታገዱ የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ዜጎችን ለማወቅ የጉዞ ወረቀቶችን በጥልቅ ክትትል ማየት የግድ ይላል። ውስብስብ የሆኑ የጉዞ መስመሮች (በተለይም ወዳጅ በሆኑ እንደ ሶርያ እና ቻይና ያሉ ሀገራት) ከአለም አቀፍ ጉዞ የታገዱ ሰዎችን ለመለየት ሊረዳ ይችላል።

### 5.2 ከሌሎች ድርጅቶቸ ጋር ያለን ግንኙነት መመርመር

ያልተማከሉ ኮርፖሬት ሞዴሎች ስልት፣ ከፊት ያሉ ድርጅቶች እና ቅርንጫፎች፣ ድርጅቶችን በሌሎች ሀገራት ስራዎች ውስጥ መደበቅ፣ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ያለን ግንኙነት መመርመር እንደሚገባ ያሰምርበታል (ይህም ጥያቄ ውስጥ ያለው ሀገር አቅሙ የሚፈቅድ ከሆነ ነው)። በተባበሩት መንግስታት ለማዕቀብ በተፈረጁ ግለሰቦች፣ ተቋማት፣ እና ሌሎች ድርጅቶች ላይ ትኩረት እንዲደረግ ይመከራል፣ ይህም በአንድ ድርጅት እና በተፈረጀ ድርጅት መካከል ግንኙነት እንዳለ ለማወቅ ነው።

Enrico Carisch
ስልክ ቁጥር፡ (610) 390 9541
2142
Rico.carisch@comcapint.com

www.comcapint.com
110 West 94 Street 2-D
New York፣ NY 10025

Loraine Rickard-Martin
ስልክ ቁጥር፡ (917) 715
loraine፡፡rickard-martin@comcapint.com

### 5.3 በሰሜን ኮሪያ ላይ የተጣለው ማእቀብ መከበር ላይ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ማሻሻል

በጥርቅም ኩባንያዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ ስልቶች በማጭበርበር እና ሚስጥራዊነት ላይ የተመረኮዙ ናቸው። ምናልባትም የእነዚን ስልቶች ውጤታማነት ለመቀነስ ከሁሉም የተሻለው መንገድ በሚጠረጠሩ የሰሜን ኮሪያ (DPRK) ስራዎች ላይ ለተባበሩት መንግስታት ሪፖርት ማድረግን ከፍ ማድረግ ነው። ተጨማሪ ግልጽነት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ለተለያዩ አባል ሀገራት የተሻለ መረጃን መስጠት እና ሰሜን ኮሪያ (DPRK) ማእቀቦችን ለመጣስ የምታደርገውን ጥረት ማሰናከል እንዲቻል ያደርጋል።

### 5.3 አፍሪካ ሀገራት ላይ በተጣለ ማእቀብ ጥሰት ላይ ልዩ ትኩረት ይደረግ

ኮሚድ /KOMID/ ሱዳን ውስጥ የነበረው እንቅስቃሴ ተቋማት በሰሜን ኮሪያ (DPRK) ላይ የተጣለውን ማእቀብ ብቻ ሳይሆን በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ላይ የተጣለውን ማእቀብም ለመጣስ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ (ከውሳኔ 1591፣ ዳርፉር ላይ የሚያበቃ የጦር መሳሪያዎች ማእቀብ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጸጥታው ምክር ቤት ጥሏል)። ኮሚድ /KOMID/ ለሱዳኑ ወታደራዊ ኢንዱስትሪያል ኮርፖሬሽን የጦር መሳሪያ ማቅረቡ ውሳኔ 1591 እንዲጣስ ሊያደርግ ይችላል)። ከአንድ በላይ ማእቀብ እንዲጣስ የሚያደርጉ ስራዎች ለአንድ ሀገር መልካም ስም መጥፋት ትልቅ ምክንያት ናቸው። እናም፣ የተቀመጡትን የተለያዩ ማእቀቦች በትክክል መረዳት ወሳኝ ነው።

### 5.4 የማእቀቦችን እና ጥሰቶችን ምድብ መፍጠር

በፊት ከነበረ ነጥብ ጋር በተያያዘ፣ የአንድ ተቋም ስራ በሰሜን ኮርያ እና ድርጅቶቹ ላይ የተጣለውን ከአንደ በላይ የሆነ ማእቀብ የሚጥስ ሊሆን ይችላል። ውስብስብ የሆኑ ተቋማት ስራዎችን በተሻለ ለመረዳት ሁሉንም ማእቀቦች መረዳት፣ የትኞቹ እንደተከለከሉ ማብላላት እና የሚሞከሩ ጥሰት እንቅስቃሴዎች ያላቸውን አንድምታ ከግምት ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ ነው። ይህም አንድ ሀገር ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ማእቀቦች አንጻር ያለውን መረዳት እንዲያሳድግ የሚሰራ ሲሆን ይህም በተራው ሰሜን ኮሪያ (DPRK) ማእቀቦችን ለመጣስ የሚታደርገውን ጥረት ለመለየት ይረዳል።

### ስለ ካትሪን ክራንዝ /Kathrin Kranz/

| | |
|---|---|
|  | ካትሪን ክራንዝ በሰላም ጥናት እና ፖለቲካዊ ሳይንስ ላይ ከኖትር ዳም ዩንቨርሲቲ የዶክትሬት ዲግሪ ያላት ሲሆን ከለንደን ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ እና ፖለቲካል ሳይንስ በሕዝባዊ አለም አቀፍ ሕግ LL.M. አላት። ምርምርዋ በአለም አቀፍ የጦር መሳሪያ ንግድ፣ የምጣኔ ሀብት ማእቀቦች እና አለምአቀፍ ተቋማት ላይ ትኩረት ያደርጋል። |

[1] “የኩባንያ ጥርቅሞች” *OED Online*. ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፤ June 2018.
[2] የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት። “በውሳኔ 1874 (2009) መሰረት የተቋቋመው የባለሙያዎች ቡድን የተርም አጋማሽ ዘገባ”። ሴፕቴምበር 5፣ 2018. http://www.un.org/ga/search/view_doc.asp?symbol=S/2017/742, ማጠቃለያ
[3] አንድራ አብራሐሚያን፤ “ማእቀብ እና ንግድ በሰሜን ኮሪያ ውስጥ፡ ከማይናማር የተገኘ ትምህርት፣” ፌብሩዋሪ 28፣ 2018፣ https://www.38north.org/2018/02/aabrahamian022818/
[4] The Economist “From Planes to Mackerel (ከ ፕሌንስ እስከ ማከሬል) አዲስ የኩባንያ ጥርቅሞች ፍልፍል ሰሜን ኮሪያን ለማነቃቃት እየረዳት ነው። ጃንዋሪ 25፣ 2018

[5] Ibid፡ The Economist፣ 2018
[6] Ibid. The Economist፣ 2018
[7] Ibid፡ አብራሃሚያን፣ 2018
[8] የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ድጋፍ ሰጪ አካላት፣ በጸጥታው ምክር ቤት ኮሚቴ በዉሳኔ 1718 (2006) መሰረት የተቋቋመ "ግሪን ፓይን አሶሺየትድ ኮርፖሬሽን" ሜይ 2፣ 2012። https://www.un.org/sc/suborg/en/sanctions/1718/materials/summaries/entity/green-pine-associated-corporation
[9] የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት። "ዝርዝሩ በጸጥታው ምክር ቤት ዉሳኔ 1718 (2006) መሰረት የተዘጋጀና የሚመራ ነው። ሜይ 24፣ 2016. https://scsanctions.un.org/fop/fop?xml=htdocs/resources/xml/en/consolidated.xml&xslt= htdocs /resources/xsl/en/dprk.xsl.
[10] የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት የኤክስፐርቶች ቡድን የመጨረሻ ሪፖርት፣ በጸጥታው ምክር ቤት ዉሳኔ 1985 (2011) መሰረት፣ ጁን 14፣ 2012. http://www.un.org/ga/search/view_doc.asp?symbol=S/2012/422፣ ቅጥያ X
[11] Hugh Griffiths በ David McKenzie እና Brent Swails "Statues and ammunition (ሀውልቶች እና ጥይት)፡ North Korea's Africa connections (የሰሜን ኮሪያና የአፍሪካ ትሥሥር) በሚለው ሪፖርት ላይ የሰጠው አስተያየት፣" *CNN*፣ ዲሴምበር 15፣ 2017. https://edition.cnn.com/2017/10/22/africa/north-korea-africa/index.html
[12] Ibid፡ CNN, 2017; "Treasury Targets Chinese and Russian Entities and Individuals Supporting the North Korean Regime (የሰሜን ኮሪያን መንግስት የሚረዱ የቻይና እና የሩሲያ ተቋማት እና ግለሰቦች)፣" US Department of the Treasury Press Center (የአሜሪካ የገንዘብ ሚኒስቴር የፕሬስ ማእከል)፣ አገስት 22፣ 2017። https://www.treasury.gov/press-center/press-releases/Pages/sm0148.aspx
[13] "የጸጥታው ምክር ቤት ውሳኔ 2371 (2017)ን በአንድ ድምጽ በማጽደቅ፣ በኮሪያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ላይ ያሉ ማዕቀቦችን አጠነከረ፣" *የተባበሩት መንግስታት ስብሰባዎች ሽፋን እና ጋዜጣዊ መግለጫዎች፣* አገስት 5፣ 2017። https://www.un.org/press/en/2017/sc12945.doc.htm
[14] የኤክስፐርቶች ቡድን የመጨረሻ ሪፖርት፣ በዉሳኔ 2094 (2013)፣ S/2014/147 መሰረት (ማርች 6፣ 2014) http://www.un.org/ga/search/view_doc.asp?symbol=S/2014/147 ገጽ፡ 119
[15] Ibid፡ አንቀጽ፡ 121
[16] የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት፤ ሰነድ S/2018/171። "በዉሳኔ 2345 (2017) መሰረት የቀረበ የኤክስፐርቶች ቡድን የመጨረሻ ዘገባ።" ማርች 5፣ 2018.http://www.un.org/ga/search/view_doc.asp?symbol=S/2018/171/ Corr.1፣ አንቀጽ፡ 116
[16] Ibid፡ S/2017/150፣ አንቀጽ፡ 116
[17]የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ድጋፍ ሰጪ አካላት፣ በጸጥታው ምክር ቤት ኮሚቴ ዉሳኔ 1718 (2006) መሰረት የተቋቋመ፣ የምስራቅ ምድር ባንክን /Bank of East Land/ መመዝገቢያ ምክንያት ገለጻ፣ አክቶበር 29፣ 2014። https://www.un.org/sc/suborg/en/sanctions/1718/materials/summaries/entity/bank-of-east-land
[18]የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት፤ ሰነድ S/2017/150 "በውሳኔ 1874 (2009) መሰረት የተዘጋጀ የኤክስፐርቶች ቡድን ዘገባ።" ፌበሩዋሪ 27፣ 2017። http://www.un.org/ga/search/view_doc.asp?symbol=S/2017/150, table 9
[19] የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ድጋፍ ሰጪ አካላት፣ የቀናጀው የተባበሩት መንግስታት ጸጥታ ምክር ቤት ማእቀብ ዝርዝር። https://scsanctions.un.org/consolidated/#alqaedaent
[20] የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ደጋፊ አካላት፣ የጸጥታዉ ምክር ቤት ኮሚቴ፣ በዉሳኔ 1718/2006/ መሰረት የተቋቋመ "ኦሽን የባህር ትራንስፖርት አስተዳደር ኩባንያ /Ocean Maritime Management Company/" OMM)፣" አክቶበር 29፣ 2014። https://www.un.org/sc/suborg/en/sanctions/1718/materials/summaries/entity/ocean-maritime-management-company%2C-limited-%28omm%29
[21] የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት የኤክስፐርቶች ቡድን ሪፖርት፣ በጸጥታው ምክር ቤት ዉሳኔ 1874 (2009) መሰረት፣ ፌብሩዋሪ 23፣ 2015፣ http://www.un.org/ga/search/view_doc.asp?symbol=S/2015/131፣ አንቀጽ፡ 131
[22] የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታ ምክር ቤት፤ ሰነድ S/2016/157። "በዉሳኔ 1874 (2009) መሠረት የተዘጋጀ የኤክስፐርቶች ቡድን ዘገባ።" ፌበሩዋሪ 24፣ 2016። http://www.un.org/ga/search/view_doc.asp?symbol=S/2016/157፣ አንቀጽ፡ 101.
[23] Ibid፡ S/2017/150፣ አንቀጽ፡ 103-104 እና ቅጥያ 70
[24] Ibid፡ S/2017/150፣ አንቀጽ፡ 110-112
[25] Ibid፡ S/2017/742፣ አንቀጽ፡ 50
[26] Ibid፡ S/2017/742፣ አንቀጽ፡ 29
[27] Ibid፡ S/2018/171፣ አንቀጽ፡ 142
[28] የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት። "ዉሳኔ 2321 (2016). በኖቬምበር 30፣ 2016 በ 7821ኛው ጉባኤው ላይ በጸጥታው ምክር ቤት የጸደቀ።" http://undocs.org/S/RES/2321(2016)፣ ቅጥያ አንድ
[29] Ibid፡ S/2018/171፣ አንቀጽ፡ 122
[30] Ibid፡ S/2017/150፣ አንቀጽ፡ 106

31 ዲክላን ዋልሽ "የሰሜን ኮሪያን ሚሳይሎች መግዛት ይፈልጋሉ? ለካይሮ ኢ.ምባሲ ይደዉሉ።" *The New York Times*፣ March 3፣ 2018። https://www.nytimes.com/2018/03/03/world/middleeast/egypt-north-korea-sanctions-arms-dealing.html፣ እና ibid፡ S/2017/150፣ ሰንጠረዥ 3.
32 በ Andrea Berger "ትራምፕ ሱዳንን (እና ዓለምን) በሰሜን ኮሪያ (DPRK) ምክንያት አስጠነቀቀ" በሚለው ውስጥ የተጠቀሰ *Arms Control Wonk* ጁላይ 12፣ 2017። https://www.armscontrolwonk.com/archive/1203587/trump-puts-sudan-and-the-world-on-notice-over-dprk/
33 Ibid፡ S/2018/171፣ አንቀጽ፡ 85
34 Ibid፡ S/2017/742፣ አንቀጽ፡ 23
35 Ibid፡ S/2016/157፣ አንቀጽ፡ 108
36 Ibid፡ S/2017/150፣ አንቀጽ፡ 175
37 Ibid፡ S/2017/150፣ አንቀጽ። 182
38 Ibid፡ S/2016/157፣ አንቀጽ፡ 94
39 Ibid፡ S/2018/171፣ አንቀጽ፡ 96
40 Ibid፡ S/2018/171፣ አንቀጽ፡ 144
41 Ibid፡ S/2017/171፣ አንቀጽ፡ 164 እና ቅጥያ 43
42 Ibid፡ S/2018/171፣ አንቀጽ፡ 162
43 Ibid፡ S/2015/131፣ አንቀጽ፡ 155
44 Ibid፡ 1718 የማእቀቦች ዝርዝር
45 Ibid፡ S/2017/150፣ ሰንጠረዥ 10።
46 Ibid፡ S/2017/150፣ አንቀጽ፡ 167፣ 172፣ 173
47 Ibid፡ Walsh፣ New York Times.
48 Ibid፡ Walsh፣ New York Times.
49 Ibid፡ S/2017/150፣ አንቀጽ፡ 25
50 Ibid፡ S/2017/150፣ አንቀጽ፡ 207
51 Ibid፡ S/2017/150፣ አንቀጽ፡ 208
52 Ibid S/2017/150፣ ሰንጠረዥ 10 እና 11
53 Ibid፡ S/2017/150፣ ሰንጠረዥ 8
54 ለምሳሌ፣ በሰሜን ኮሪያ (DPRK) የመንግስት ደህንነት መኮንን ሚኒስቴር የ Ri Won Hoን ፓስፖርት ቁጥር ላይ ያለውን አለመጣጣም ማየት ይቻላል ይህም በተቀናጀው ማእቀብ ዝርዝር እና S/2017/150 መካከል ያለ ልዩነት ነው። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት፣ የቀናጀው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታ ምክር ቤት ማእቀብ ዝርዝር https://scsanctions.un.org/en/?keywords=&per-page=2500&sections=s&sections=s&sort=id&includes=&excludes=&committee=&nationality=&reference_from=&reference_to=. Ibid፡ S/2017/150፣ ሰንጠረዥ 8.
55 Ibid፡ S/2018/171፣ አንቀጽ፡ 161
56 Ibid፡ S/2017/742፣ አንቀጽ፡ 57
57 አልዩም አልጃዲድ ጋዜጣ፡ (ካይሮ ውስጥ ያለው የሰሜን ኮሪያ አምባሳደር በህገወጥ የመሳሪያ ዝውውር ምክንያት ከሀገሪቱ ሊባረር ነው) ማርች 22 2016። http://www.elyomnew.com/news/worldwide/2016/03/22/48128#.WwG40UiFPIU
58 Ibid. S/2017/150፣ አንቀጽ፡ 163
59 Ibid፡ S/2015/131፣ አንቀጽ፡ 128 እና 129
60 Donia Alwatan፣ https://www.alwatanvoice.com/arabic/news/2016/01/18/852255.html. ጃንዋሪ 18፣ 2016 ዓ.ም
61 Ibid፡ S/2016/157፣ ሰንጠረዥ 8 እና አንቀጽ፡ 175.
62 Ibid፡ S/2018/171፣ ቅጥያ 43
63 Ibid፡ S/2016/157፣ አንቀጽ፡ 108

Enrico Carisch
ስልክ ቁጥር፡ (610) 390 9541 2142
Rico.carisch@comcapint.com

www.comcapint.com
110 West 94 Street 2-D
New York፣ NY 10025

Loraine Rickard-Martin
ስልክ ቁጥር፡ (917) 715
loraine፡፡rickard-martin@comcapint.com